Abrham Yohanes https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፬
አዲስ አበባ ነሐሴ ፬ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 74
ADDIS ABABA, 10th, August, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፪/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የሚናማታ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ......ገጽ ፲፪ሺ፯፻፳፬

## CONTENT

PROCLAMATION No.1222/2020

Minamata Convention Ratification Proclamation…page 12724

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፪/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

### የሚናማታ ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የሚናማታ ስምምነት ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም በኩማሞቶ ጃፓን ስምምነት የተደረሰበት በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ስምምነቱን ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም የፈረመው በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሀምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### PROCLAMATION NO. 1222/2020

### PROCLAMATION TO RATIFY THE MINAMATA CONVENTION

**WHEREAS,** the Minamata Convention was adopted in Kumamoto, Japan on 10th October 2013;

**WHEREAS,** the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia signed the Convention on 10th October 2013;

**WHERE AS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 14th day of July , 2020;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

Abrham Yohanes https://chilot.me



**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የሚናማታ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፪/፪ሺ፲፪ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪.<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሰት ጥቅምት ፲፫ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም የተፈረመው የሚናማታ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል::

**፫.<u>መግለጫ</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ፣ ደንና፣ የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር በስምምነቱ አንቀጽ ፬፣ ፭ እና ፮ መሰረት የሚቀርቡ የእፎይታ ጊዜ እና የሜርኩሪ አጠቃቀም መግለጫዎችን ለስምምነቱ ጽህፈት ቤት ያቀርባል፡፡

**፬.<u>አስፈጻሚ አካል</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ፣ ደንና፣ የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፕሮቶኮሉን የማስፈጸም እና የመከታተል ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

**፭.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፬ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Minamata Convention Ratification Proclamation No. 1222/2019."

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Minamata Convention signed by the Federal Democratic Republic of Ethiopia on 10th day of October ,2013 is hereby ratified.

**3. <u>Declaration</u>**

The Environment, Forest, and Climate Change Commission of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall after consulting the pertinent government organs deposit at the Secretariat of the Convention the exemptions and proposals on the reduction of the use of Mercury pursuant to Articles 4,5 and 6 of the Convention.

**4. <u>Implementing Organ</u>**

The Environment, Forest, and Climate Change Commission of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is given the responsibility to cooperate with other relevant organs to implement and follow-up this Convention.

**5. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 10th day of August ,2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**